# አሥመራ ያለ!

ተዋጊው ሁሉ አሥመራ ገብቶ:

መወጣት አልቻለም እራሱ ከድቶ:

የሚገርምና የሚያሳዝነው:

መሀል ከተማ አሥመራ ያለው:

መጣሁ እያለ የሚፎክረው:

ወይ ወደፊት አይሄድ አይራመደው:

ወይ አይቀርበት ትግሉን አይተወው:

አሥመራ ገብቶ መጮህ ምንድነው?

ድንበር አቋርጦ መጣሁኝ ካለ:

ያመታት ትጥቁ ታድያ የታለ?

ሌሎች በሰሩት እሚፎልለው:

ያልዘራውን ዘር ሊያጭድ ያቀደው:

የሰውን ልፋት የኔ ነው ያለው:

ከየት መጥቶ ነው ኧረ እሱ ማነው?

ካፋፍ ላይ ቆሞ ዘራፍ እያለ:

አሁን የት ገባ ያ አሥመራ ያለ!

እኛ አንጣላ ከማንም ጋራ:

ሠርቶ ማሳየት ለጠላት ጎራ:

ሆኗል ቃላችን ገሎ የመሞት:

ታጋይ ነን እኛ ላንድ ነፃነት!

ሀገራችን ላይ እየፎከሩ:

ከዳሩ ቆመው የያቃጥሩ:

ከሀዲ ሆዳም የት ተሰወሩ:

ቅጣቱ ላይቀር በየ መንደሩ:

ከመሸገበት ከጉራንጉሩ:

ፋኖ አንዴ መጥቷል ለመመንጠሩ::

በሀገራችን ለምናረገው:

እኛም አንፎክር አንል ይሄ ነው::

መልስም አንሰጥ ጥያቄም የለም:

መጥቶ መሄድ ነው የምን ማጉረምረም!

ድል የኢትዮጵያ ህዝብ ነው!

EPNP.INFO